# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 2 ቁጥር 70 ታህሳስ 28 ቀን 2013ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ‹ ‹ ጥቂት ዓመታት ከታገስን ኢትዮጵያ መልካም ትሆናለች › ›

ስለሺ ሐጎስ (ጋዜጠኛ)



# ቆይታ

## ‹‹ጥቂት ዓመታት ከታገስን ኢትዮጵያ መልካም ትሆናለች››

### ስለሺ ሐጎስ (ጋዜጠኛ)

ብዙዎች በሕትመት ሚዲያ ቆይታው ያስታውሱታል፡፡ የቼንጅ መጽሔት መስራችና ማኔጂንግ ኤዲተር ነበር፡፡ በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሥር ትታተም የነበረችው የሚሊየኖች ድምጽ ጋዜጣ ላይም ዋና አዘጋጅም ሆኖ ሰርቷል፡፡ ኢትዮ ምህዳር፤ ሐብል እንዲሁም አዲስ ከተማ በተሰኙት የህመት ሚዲያዎች ላይም ከአምደኛነት እስከ ዋና አዘጋጅነት ያሉ ኃላፊነቶች ወስዶ ሰርቷል። የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ አባልና የብሔራዊ ምክር ቤት አባልም ሆኖ አገልግሏል፡፡ የዛሬው የዜጎች መድረክ የ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳ ነው፡፡ እንግዳችን ጋዜጠኛ ስለሺ ሐጎስ ይባላል፡፡ ቆይታችንን ለአንባቢዎቻችን በሚመች መልኩ ከድምጽ ወደ ጽሁፍ ለውጠን እንደሚከተለው አሰናድተንዋል፡፡ መልካም ንባብ!



*በቅድሚያ አሁን ለምናደርገው ቆይታ ፈቃድህን ስለሰጠኸኝ አመሰግናለሁ። አንዳንድ ሰዎች ስለሺ ምነው ጠፋ ይላሉ። ጠፍሃል ልበል?*

አረ እኔ ከሚጠፋት ወገን አይደለሁም (ሳቅ...)

*እሺ ጥያቄውን ላስተካክል... ከሚድያው ራቅ ብለሀል፡፡ ከዚህ በፊት በስፋት ትሳተፍበት በነበረው ማህበራዊ ሚዲያው ላይም የለህም ምክኒያትህ ምንድ ነው?*

ባክህ አትቀልድ፤ አሁን እኮ ምነው ከሚዲያው ራቅክ? ተብሎ የሚጠየቅበት ጊዜ አይደለም፡፡ ከሚድያው ስለራቅህ አመሰግናለሁ ነው የሚባለው፡፡ ይልቅ አክቲቪስት እና ጋዜጠኛ ነን እያሉ የሚዘባርቁ አንዳንድ ሰዎችን ጠርተህ መች ነው ከሚድያ የምትርቁት? ብለህ መጠየቅ ነው የሚሻልህ፡፡

*ለምን እንዲህ አልህ?*

አሁን ሀገራችን ካለችበት ሁለንተናዊ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ወደ አደባባዩ ስትወጣ እጅግ ጥንቃቄ በተሞላው ኃላፊነት የምትናገርበት፣ የምትናገረው ነገር የሚያመጣው ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ ካልሆንክ ዝም በማለት ለሀገርህ ውለታ የምትውልበት ወቅት ላይ ነው ያለነው፡፡ በዚያ ላይ የተናጋሪ ችግር የለም፡፡ ብዙ አፎች አሉ፤ የማይሰሙ ትልልቅ ጆሮዎች አሉ፡፡ እዚህ ውስጥ ገብቶ መዋኘት መደናቋቆር ነው የሚሆነው፡፡ በዚህ ወቅት የግድ ማለት ያለብህ ጠቃሚ ነገር ከሌለህ ዝምታን መምረጥ ማለት ለሀገርህ ውለታ መሥራት ማለት ነው፡፡

*ያለፉትን ሶስት ዓመታትና ለውጡን እንዴት ትገመግመዋለህ?*

ኢትዮጵያ በጥሩ ሀዲድ ላይ እየተጓዘች እንዳለ ነው የሚሰማኝ፡፡ ይሁን እንጂ በእነዚህ ዓመታት ካሳለፍነው መከራ፣ ከተከፈለው የንጹኃን ህይወት፣ ከተፈናቀለው ዜጋ በተጨማሪ ወደፊት የሚጠብቁን አንዳንድ ተግዳሮቶች ቀላል ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ያም ሆኖ ብሩህ ጊዜ ይታየኛል። መንግሥት ከወሰዳቸው እርምጃዎች መካከል በአንዳንድ ተቋማት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ለማድረግ ያደረገውን ሙከራ አደንቃለሁ፡፡ እንደ ምርጫ ቦርድና እንደ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሁሉ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ የታሰበውን ለውጥ የሚመራ ጥሩ ሰው ቢያገኙለት ኖሮና ለሚዲያው የኋሊት ጉዞ የሆነ መፍትሄ ቢበጅለት ከዚህ በላይ መልካም ይሆን ነበር፡፡ በአጠቃላይ ጥቂት ዓመታቶችን በጽናት ካለፍን ኢትዮጵያ በመልካም ሁኔታ ላይ የምትገኝ ተፎካካሪ ሀገር ትሆናለች የሚል እምነት አለኝ፡፡

*የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ሕግ ለማስከበር በሚል በሕወሓት ላይ የወሰደው እርምጃ ብዙ ትችት እየደረሰበት ነው፡፡ ባንተ ግምገማ እንዴት ትገልጸዋለህ?*

ሕግ ለማስከበር የሚለውን ስያሜ ተወው፡፡ ሕግ ስለተጣሰ ብሎ ወይም ሕወሓት በሕዝቡ ላይ ሲወስድ የነበረውን ሕገ ወጥ እርምጃ ለማስቆም ብሎ የዘመተ ሠራዊት የለም፡፡ የሠራዊቱን አባላት ገድለው በራሱ ላይ ጦርነት ስለከፈቱበት ነው ወደ ሕወሓት የተዘመተው፡፡ እንጂማ ሕወሓት ከአዲስ አበባ ተባርራ ትግራይ ከመሸገችበት ዕለት አንስቶ እንደ ላጲስ ተፈርፍራ እስካለቀችበት ጊዜ ድረስ ሕገ ወጥነትን እንደ አክስጅን ነበር የምትተነፍሰው፡፡ የዚያን ጊዜ ማንም የተናገራት አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ ማለዳም ቢሆን አልረፈደም፡፡ መጨረሻም የሚሆነው ሆነ፡፡ ተገቢም ነበር፡፡

በሕወሓት ላይ የተወሰደውን እርምጃ ተከትሎ ብዙ ዓይነት ትችቶች ነው የሚቀርቡት፡፡ በእኔ እምነት በጦርነቱ ሂደት ሳይሆን መንግሥት ከዚህ በኋላ በትግራይ አስተዳደር ሂደት ውስጥ የሚፈጥራቸው ነገሮች ናቸው ለትችት ሊበቁ የሚችሉት፡፡ እሱ ላይ ትችት ለመሰንዘር ጊዜው በጣም ገና ነው፡፡

*በቤንሻንጉል ክልል በተለይ በመተከል አካባቢ ተደጋጋሚ የፀጥታ ችግር ይስተዋላል፡፡ የዜጎች ሕይወትም እንደ ቅጠል እየረገፈ ይገኛል ፡፡ ለዚህ ችግር በምን መልክ ነው ዘለቄታዊ መፍትሔ ማበጀት የሚቻለው?*

በቤንሻንጉል ክልል የሚስተዋለው ሁኔታ እንቆቅልሽ ይመስላል፡፡ አካባቢው ላይ ይህ ነው የሚባል ፖለቲካዊ ጥያቄ አይሰማም፤ ለዜጎች ሞት ኃላፊነት የሚወስድና በአካባቢው የሚንቀሳቀስ ግልጽ ጠላት አታገኝም፤ ግን የጅምላ ግድያ ዜናዎች ትሰማለህ። በአንድ ቀን ከ200 በላይ ሰዎች ሲሞቱ ይህ ነው የሚባል ገዳይ የላቸውም፡፡ ነገሩ እንቆቅልሽ ይመስላል።

ዘግይቶም ቢሆን መንግሥት አሁን እየወሰደ ያለው ደፈር ያለ እርምጃ የሚበረታታ ቢሆንም ችግሩን የሚያስቆመው አይመስለኝም፡፡ እንዳይሆን እፀልያለሁ፤ ግን አሁንም ይህ ድርጊት (የዜጎች ሞትና መፈናቀል) ሊቀጥል ይችላል፡፡ በኔ ዕምነት ነገሩን ማስቆም የሚቻለው የችግሩን ሰንኮፍ መንቀል ከተቻለ ብቻ ነው፡፡

*የችግሩ ሰንኮፍ ምንድነው?*

የችግሩ ዋና ምንጭ ከታላቁ ሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅ በኋላ የመተከል ዞን ከቤንሻንጉል ክልል ጋር የመሰንበቱ ነገር ጥያቄ ውስጥ ሊወድቅ ይችላል የሚል ስጋት መኖሩ ነው፡፡

*እስኪ በደንብ አብራራው*

ጥሩ፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚፈጥረው ሃይቅ የሚተኛው በክልሉ ወገብ ላይ ነው። እንደምታውቀው በቤኒሻንጉል ክልል ስር ያሉት ሁለቱን ትንንሽ ልዩ ወረዳዎች ትተህ በዋናነት አሶሳ፣ ካማሺና መተከል የሚባሉ 3 ዞኖች አሉ። ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚፈጠረው ወደ 1,874 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ሐይቅ ዋና ከተማው ያለበትን አሶሳ ዞንን ጨምሮ አንደኛውን ልዩ ወረዳና የካማሼን ዞንን ወደ ታች አርጎ የመተከልን ዞንና ቀሪውን አንድ ልዩ ወረዳ ወደ ላይ በማድረግ ክልሉን ለሁለት ይቆርጠዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ ላይ የቀረውን የመተከል ዞን ከቤንሻንጉል ጋር ማቆየት የምትችለው እጅግ ውድ የሆነ መሰረተ ልማት ገንብተህ ብዙ ወጪ የሚያስወጣ የውሃ ትራንስፖርት መጠቀም የቻልክ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ያ ደግሞ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ስለዚህ ከግድቡ በኋላ የመከተል ዞን ዕጣ ፈንታ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ ለችግሩ ምንጭ ሆኖ ነው የሚታየኝ፡፡

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝደንት ሲናገር ሰምተኸው ከሆነ በክልሉ ላይ ያለውን የሕዝብ ብዛት ቁጥር ከፍ ለማድረግ ጥረት እያደረገ መሆኑን ሰምተናል፡፡ የአማራ ክልላዊ መንግሥትም ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ ጠይቋል፡፡ በአካባቢው ያሉ አንዳንድ ሀይሎችም የዕጣ ፈንታ ጥያቄ መወላወሉ ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ጥቃቱና ሽሚያው በመንግሥታዊ መዋቅር ጭምር የሚታገዝ ውስብስብ ችግር ነው፡፡ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቤንሻንጉልን፣ የኦሮሚያንና የአማራን ክልላዊ መንግሥታት ቁጭ አድርጎ አወያይቶ ከአባይ ግድብ ፍጻሜ በኋላ በክልሉ ላይ በሚፈጠረው መልከአምድራዊ ለውጥ ሳቢያ የመተከል ዞን ዕጣፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ችግሩን በዘለቄታዊነት የሚፈታ አይመስለኝም፡፡

መቶ ሰው ስትገድል መቶሺህ ሰው ታፈናቅላለህ፡፡ የግድያው አላማ እኮ መቶ ሰው ገድሎ መቶሺህ ሰው ማፈናቀልና በውጤቱ የራስህን ቁጥር እንኳ ማብዛት ቢያቅትህ ሌላውን ቁጥር በመቀነስ አካባቢውን በበላይነት መቆጣጠር ነው።

*አሁን ደግሞ ኢዜማ ላይ ያለህን ምልከታ አካፍለን፡፡*

እግዚአብሔርና ሁኔታዎች ፈቅደው ምርጫው የሚከናወን ከሆነ ልመርጣቸው ከምችለው ፓርቲዎች


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ታህሳስ 28 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

መሀከል አንዱ ኢዜማ ነው፡፡ ለነገሩ ምርጫው የሚከናወነው በብልፅግናና በኢዜማ መሀከል ነው፡፡ እኔም ልመርጥ የምችለው ከሁለቱ አንዱን ነው፡፡ እስካሁን አልወሰንኩም፡፡

*ውሳኔ ላይ ያልደረስከው ለምንድነው?*

ሁለቱም ፓርቲዎች የየራሳቸው ጥንካሬዎች አላቸው፡፡ ብልፅግና ኢሕአዴግን ያፈረሰ ሕወሓትን የደመሰሰ ፓርቲ ነው፡፡ ኢዜማ ደግሞ የማምናቸውና ራሳቸውን በፖለቲካ ሂደት ፈትነው በፅናት የወጡ ምርጥ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ያሉበት ስብስብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱም የየራሳቸው ድክመት አላቸው፡፡

*የብልፅግና ድክመት ይቆየንና የኢዜማን ድክመት ግለፅልን፡፡*

ኢዜማ አንደኛ የፕሮግራም ግልፅነት ይጎድለዋል ባይ ነኝ፡፡ ፕሮግራሙን በደንብ ለማየት ሞክሬያለሁ ፡፡ በግለሰብ ነፃነትና በማኅበራዊ ፍትህ መሀከል የሚዋልል ሆኖ ነው ያገኘሁት ፡፡ እነዚህ ሁለት ትይዩ ሀሳቦች የማይታረቁ አይደሉም፡፡ ጥያቄዬ ኢዜማ እንዴት እንደሚያስታርቃቸው አልነገረንም፡፡ ስለማኅበራዊ ፍትህ ሲያወራም እኔ የት እንዳለሁ አልነገረኝም፡፡

*ኢዜማ በፕሮገራሙ ላይ ማኅበራዊ ፍትህ ሲል በራሳቸው ስንፍና ሳይሆን በገበያ ኢኮኖሚ ተገፍተው ለድህነት የተዳረጉ ዜጎችን እንደሚታደግ አስቀምጧል፡፡*

እኮ እኔ የት ነው ያለሁት? ከግፉአን ወገን ነኝ ወይስ ከገፊዎች? አላውቅም ፡፡ በግልፅ ከገለፃቸው ቡድኖች ውስጥ አልካተተም፡፡ በፕሮግራሙ ላይ ሴቶች ብሏል፤ ሴት አይደለሁም፤ ሕጻናት ብሏል ፡፡ ሕጻን አይደለሁም፡፡ አረጋውያን ብሏል፡፡ አረጋዊ አይደለሁም፡፡ አካል ጉዳተኞች ብሏል፤ አካል ጉዳተኛ አይደለሁም ፡፡ በእርግጥ ወያኔ አካል ጉዳተኛ ልታደርገኝ ሞክራ ነበር፡፡ ግን እግዚአብሔር ይመስገን፤ ድኛለሁ፡፡ የት ምድብ ውስጥ ነኝ ንገረኝ ፡፡ ከረጢቶቹ በሙሉ አይበቁኝም፡፡ አንድ ነጋዴ ወይም አንድ ገበሬ በገበያ ኢኮኖሚ የተገፋ ነው ወይስ የገፋ መስፈሪያውን ግልፅ አላደረገም፡፡

እኔ በኢትዮጵያ ውስጥ አድሬስ ያልተደረገ ማንነት የግለሰብ ማንነት ነው ብዬ ነው ማምነው፡፡ ቡድን አይስማማኝም። ቡድን ቡድን ነው፡፡ በጾታ መደብከኝ በብሔር መደብከኝ በኢኮኖሚ ደረጃ መደብከኝ ቡድን ቡድን ነው፡፡ ኢዜማ ዜጎችን በቡድን ለማስቀመጥ መታተር ነበረበት ብዬ አላምንም፡፡ በግልፅና በማያወላዳ ሁኔታ በግለሰብ ሁለንተናዊ ነፃነትና ልዕልና ላይ ቢያተኩር ነበር የሚሻለው፡፡

*ዜጎች ብሎ አስቀምጧል፡፡ እሱ ከረጢት አይበቃህም?*

እሱ ከረጢት ያፈሳል። ምክኒያቱም በእኔ ወይም በሌላ አንድ ዜጋና ኢዜማ ማኅበራዊ ፍትህ ይገባቸዋል በሚላቸው ማኅበረሰቦች መሀከል የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ኢዜማ ምን ሊያደርግ እንደሚችል በፕሮግራሙ ላይ ግልፅ አድርጎት አታይም። ያ ቢሆን ኖሮ ይሄ ጥያቄ አይነሳም ነበር፡፡

*የዜግነት ፖለቲካና ማኅበራዊ ፍትህ አንድ ላይ የሚሄዱ አስተሳሰቦች አይደሉም እያልከኝ ነው?*

ይሄ በጣም የከረመ ክርክር ነው፡፡ ሊሄዱ ይችላሉ ብለው የሚከራከሩ አሰላሳዮች አሉ፡፡ በትይዩ ደግሞ "ማኅበራዊ ፍትህ ስትል በቅድሚያ አንዳች ፍትህ የተነፈገ ማኅበረሰብ አለ ማለትህ ነው፡፡ ፍትህ የተነፈገ ማኅበረሰብ አለ ካልክ ደግሞ የነፈገ ማኅበረሰብ አለ እያልክ ነው፡፡ በሌላ አባባል የምትወግንለትና የምትታገለው ማኅበረሰብ ክፍሎች አሉህ ማለት ነው፡፡ በዚህ መሀከል ያለ ጠባቂ የሚቀረው የግለሰብ ፍትህና ነጻነት ነው" የሚሉም አሉ፡፡

እኔ አብረው የሚሄዱ ፍልስፍናዎች አይደሉም የሚል መከራከሪያ የለኝም ፡፡ ጥያቄዬ እነዚህ ሁለት ፍላጎቶች አንድ ላይ ሲመጡ የኢዜማ ፕሮግራም እንዴት እንደሚፈታቸው በግልፅ አላስቀመጠም ነው፡፡

ሌላው ማኅበራዊ ፍትህ የሚባል ፍልስፍና ስትከተል በተለይም የኢኮኖሚ ክንፉ ላይ ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ስርጭት ያስፈልጋል እያልክ ነው፡፡ ማን ነው ሀብቱን የሚያሰራጨው? በፍልስፍናው ላይ የተመራመሩ ሰዎች መንግሥት ወደ ሀብት ስርጭት ውስጥ የሚገባ ከሆነ ሀሳቡ የሚሳካ እንደማይሆን ነው የሚከራከሩት፡፡ የኢዜማ ፕሮግራም ደግሞ መንግሥትን በሀብት አሰራጭነት ይሾመዋል፡፡

ተስፋዬ ምንድነው? በፕሮግራሙ ላይ በግልፅ ባያብራራውም ወደፊት በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎችና ሌሎች ጥናቶች ላይ አድምቶ ያያቸዋል የሚል ነው፡፡ ያኔ የሚስማማኝ ከሆነ መርጠዋለሁ፡፡ አለበለዚያ ግን ቻው በለው፡፡ (ሳቅ....)

*ብልፅግናና ኢዜማን አንድ አድርጎ የማየቱ ነገር አለ፡፡ አንዳንዶች እንደውም ነገሩን ለጥጠውት ኢዜማ የብልፅግና አጋር ነው ይሉታል፡፡ በዚህ ላይ ምን ሀሳብ አለህ?*

የሚጠበቅ ትችት ነው፡፡ ኢዜማ ከለውጡ ወዲህ በተከሰቱ ትልልቅ መንግሥትን በሚያስተቹ ሁነቶችና በመንግሥት የዕለት ተዕለት ህጸጾች ላይ ጮክ ያለ ነገር ሲያቀርብ አይስተዋልም። ከዚህ ተነስተው ትችት የሚያቀርቡ ሰዎች ላይ ምንም ጥያቄ ላነሳ አልችልም፡፡ በኔ ዕይታ ግን ይህ ከጠንካራ ጎኑ የሚቀዳ ትችት ነው፡፡

እኔን ከሚመስጡኝ የኢዜማ ጠንካራ ጎኖች አንዱ የሀገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ የገመገመበት መንገድና በግምገማው ውጤትም ራሱን ያስቀመጠበት ቦታ ነው፡፡ ከኢዜማ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለኝም፡፡ ከተግባሮቹ የምረዳው ነገር ግን ኢዜማ በሀገርና በሕዝብ ደኅንነት ጉዳይ ራሱን በኃላፊነት ቦታ ላይ ማስቀመጡን ነው፡፡

መሸቶ በነጋ ቁጥር መንግሥት የሚስታቸውን ስህተቶችና ደካማ ጎኖች እየለቀሙ ለፖለቲካ ትርፍ ማግኚያነት ላለመጠቀም መወሰኑ የሚያሳየኝ ይህንኑ ነው፡፡ የመልዕክት ሥነ ምግባሩም እንዲሁ ራሱን በኃላፊነት ላይ እንዳስቀመጠና ለውጡን በዘለቄታነት ለማስቀጠል ማገዝ እንደሚፈልግ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ዋጋ ያስከፍልሀል፡፡ ከዋጋዎቹ አንዱ ተደጋፊ፣ ተደማሪ፣ ተለጣፊ ወዘተ.... የሚለው ትችት ነው፡፡

መንግሥት አውቆም ይሁን ዘንግቶ በየጊዜው የሚስታቸው ስህተቶች ለአንድ ተፎካካሪ ድርጅት ከሰማይ የወረዱ ፍርፍሮች ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል የጆ ባይደንና የትራምፕን የሰሞኑን የአሜሪካን ምርጫ ማየት ትችላለህ፡፡ ብላክ ላይቭ ማተርስ የሚለው የጥቁሮች እንቅስቃሴና የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለጆ ባይደን መመረጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ ጆ



ባይደንን ከመረጡ 81 ሚሊየን አሜሪካውያን መሀከል 65 በመቶው በኮቪድ 19 ወረርሽኝና በጥቁሮች እንቅስቃሴ ሳቢያ በትራምፕ የተከፉ እንጂ ጆ ባይደን ይሻላል ብለው የሚያምኑ አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ የጥቁሮቹ ጥያቄም ሆነ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የትራምፕ ችግሮች አይደሉም፡፡

እንደዚህ ያሉ አትራፊ የፖለቲካዊ አጋጣሚዎችን ላለመጠቀም መወሰን የሚያሳጣህ ጥቅም አለ፡፡ ስለ ሀገር ደህንነት ሲባል እነዚህ ጥቅሞች ጥንቅር ብለው ይቅሩ ብሎ መተው ኃላፊነት ከሚሰማው ፖለቲካ ፓርቲ የሚጠበቅ ነው፡፡

ኢዜማ በዚህ ተግባሩ ኃላፊነት የሚሰማው ብቻ ሳይሆን የሀሳብ ክርክር ብቻ አቅርቤ ማሸነፍ እችላለሁ ብሎ በራሱ የሚተማመን ፓርቲ መሆኑንም ነው ያሳየው፡፡ ተቸው ካልከኝ የምተቸው ይህንን መንገድ ለምን እንደመረጠ ቢያንስ በፓርቲ ውስጥ ላሉ ኦፐሬሽናል ሥራ ላይ ለተሰማሩ አባላቱና አመራሮቹ በደንብ አስረድቶ የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ ያልቻለ እንደሆነ ነው፡፡ የሚያሰጋው ከውጪ ያለው ትችት ሳይሆን በፓርቲው ውስጥ ያሉ አባላት ፓርቲው ጥላና ከለላ እንደማይሆናቸው ካመኑ በፓርቲው ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ነው፡፡ ይህን ለአባላቶቹ ምን ያህል አስረድቷል፤ አላውቅም፡፡

*6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ግንቦት መጨረሻ ላይ እንደሚካሄድ እርግጥ ሆኗል፡፡ አንዳንድ ቡድኖች ከሕገ መንግሥት ማሻሻያ በፊት ምርጫ ማካሄድ ፋይዳ ቢስ ነው ይላሉ፡፡ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አለህ? ምርጫው ያለ ሕገ መንግሥት ማሻሻያም ቢሆን መካሄድ አለበት ብለህ ታምናለህ?*

ይህ ያልከውን ነገር ከአንተ ነው የምሰማው፡፡ ይህንን ሀሳብ ማንም ያቅርበው ማንም ብሽቅ ሀሳብ ነው፡፡ ምርጫ ማለት ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያም ይሁን ማንኛውንም ይሆናል የምትለውን ነገር ማሻሻያ መሣሪያ ነው፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ ካልተካሄደ ምርጫ ማድረግ አይገባም ማለት ነገ ምሳ ስለማልበላ ዛሬ ቁርስ አልበላም እንደማለት ነው፡፡ ለነገ ምሳ በብርታት የምትደርሰው ዛሬ ቁርስ የበላህ እንደሆነ ነው፡፡ አልያ የነገው ምሳ ላይ የምትቀርበው በሚሸሽ የምግብ ፍላጎት ነው፡፡ አትበላውም፡፡ አሪፍ ሀሳብ አይደለም ምርጫው መካሄድ አለበት፡፡

## ‹‹ እንደዚህ ያሉ አትራፊ የፖለቲካዊ አጋጣሚዎችን ላለመጠቀም መወሰን የሚያሳጣህ ጥቅም አለ፡፡ ስለ ሀገር ደህንነት ሲባል እነዚህ ጥቅሞች ጥንቅር ብለው ይቅሩ ብሎ መተው ኃላፊነት ከሚሰማው ፖለቲካ ፓርቲ የሚጠበቅ ነው፡፡ ››

*ኢዜማ ምርጫውን ለማሸነፍ ምን ማድረግ አለበት?*

ሶስት ነገሮች 1ኛ ካምፔን፣ 2ኛ ካምፔን፣ 3ኛ ካምፔን

*ምን ማለት ነው?*

አንደኛ ካምፔን ፕሮሚስ ወይም ግልፅ ያለ የመወዳደሪያ ሀሳብ፡፡ ቁልጭ ብለው የተቀመጡ የሚሸጡ ሀሳቦች፡፡ ሁለተኛ ካምፔን ስትራቴጂና የካምፔይን ግብረኃይል፡፡ ሀሳቦቹን በትክክል ለመሸጥና ለማስረዳት የሚችል ስትራቴጂና ያንን የሚያስፈፅሙ ብቁ ባለሙያዎች፡፡ ሶስተኛ የተጠቀሱትን ተግባራት ለመከወን የሚያስችል የካምፔን ገንዘብ። በእነዚህ በሶስቱ ላይ በጥሩ ሁኔታ ከተዘጋጀ ያሸንፋል፡፡

*እነዚህን ሶስቱን ማሟላት ባይችልስ ለምሳሌ በቂ ገንዘብ ባይኖረውስ?*

ደህና ሰንብት በለው፡፡

*ደህና ሰንብት ስትል?*

ሶስቱንም አሟልተህ በሚቀጥለው ምርጫ ለመወዳደር ተዘጋጅ፡፡ በዚህኛው ምርጫ ሪሶርስ አታባክን በለው።

*እኔ ማንሳት ሲኖርብኝ ያላነሳሁት ጥያቄ ካለ የማጠቃለያ ሀሳብ ለመሰንዘር መድረኩ ክፍት ነው፡፡*

አንባቢዎችህን እስካሁን ያደነቆርኳቸው ይበቃኛል፡፡ ለግብዣህ አመሰግናለሁ፡፡

ማሪሚያ፡- ባሳለፍነው ሳምንት በወጣው የዜጎች መድረክ ቅፅ 2 ቁጥር 69 እትም ላይ የ ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳ የነበሩት ከውሰር እድሪስ የኃላፊነት ቦታን የኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ኃላፊ ብለን መጥቀሳችን ይታወቃል፡፡ መሰል የኃላፊነት ቦታ እንደሌለ ለማወቅ ችለናል፡፡ ስለዚህም ይህን ማረሚያ ማውጣት አስፈልጎናል፡፡ ከውሰር እድሪስ፣ የኢዜማ ምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ናቸው፡፡ ለተፈጠረው ስህተት አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

# ነፃ ሀሳብ

ማሳሰቢያ፡- ይህ ፅሁፍ የፀሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚወክለው!
የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅን ማግኘት ቢያስፈልግ tigistyoni18@gmail.com ይጠቀሙ

# ሴት ሲበዛ ምርጫው ሰላማዊ እና ነፃ ይሆናል !

ትዕግስት ወርቅነህ (የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ)

## የሴቶች ጠንካራ የፖለቲካ ተሳትፎ የሌለበት የፖለቲካ ማኅበረሰብ አንካሳ ነው!

የጾታ ኢ- እኩልነት በስፋት በሚታይባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ከፍተኛ የሆነ የመብት ጥሰቶች እና የተለያዩ ማኅበራዊ ጫናዎች በሴቶች ላይ ይደርሳሉ፡፡ ለዘመናት በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደልማድ ተይዞ የቆየው ሴቶችን በእኩል ያለማየት እና ወደኋላ የሚያስቀር አሠራር ከየትኛውም የማኅበረሰብ የወል ስብስብ በላይ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሴቶች የሀገር ሀብት እና መልካም አጋጣሚዎች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከማድረጉም ባሻገር ሴቶች ለማኅበረሰባቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን ከፍተኛ አስተዋጽዎ ውስን እንዲሆን አድርጓል፡፡ በእርግጥ የሴቶች እና የሴቶች አመራር ያልተነካ አቅም እና ተሰጥዖ እውቅና እየተሰጠው እና እያደገ መምጣቱ የማይካድ ቢሆንም አጥጋቢ ውጤት ላይ ግን ገና አልደረሰም፡፡

ሴቶች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ያላቸው ሚና ብዙውን ጊዜ በቅጡ የማይሰላና ዋጋም የማይሰጠው ነው፡፡ በገጠር የምትኖር ሴት በቀን 16 ሰዓታትን በሥራ የምታሳልፍ ቢሆንም አስተዋጽዎዋ በኅብረተሰቡ ዘንድ ትኩረት አይሰጠውም፡፡ ይህ እውነት በተነፃፃሪ ያነሰ የሥራ ድርሻ ቢኖራትም በከተማ የምትኖር ሴትም እጣ ፋንታ ነው፡፡ በቤት ውስጥ ሥራ ተጠምደው የሚውሉ ሴቶች ውጭ ወጥተው ባለመሥራታቸው ብቻ እንደ ሥራ አጥ ይቆጠራሉ እንጂ ሥራቸው ተመዝኖ ተገቢው ቦታ ሲሰጣቸው አይስተዋልም፡፡

በየትኛውም የዓለማችን ክፍል የሕፃናት እና የሽማግሌዎች ብሎም የመላው ቤተሰብ ዋና ተንከባካቢዎች ሴቶች ናቸው፡፡ የዓለም አቀፍ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአንድ ህብረተሰብ ኢኮኖሚ እና የፖለቲካ አደረጃጀት ሲለወጥ ሴቶች ቤተሰቦቻቸውን ከአዳዲስ እውነታዎች እና ተግዳሮቶች ጋር እንዲላመዱ በመርዳት ረገድ ግንባር ቀደም ሆነው እንደሚሰሩ ያሳያል፡፡ ቤተሰብ ተረጋግቶ ሕይወቱ በደስታ እንዲቀጥል እና ልጆች በተረጋጋ ቤተሰብ ውስጥ እንዲያድጉ የሴቶች ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ እንዲሁም ልጆች ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ፣ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ የማድረጉ ከፍታኛ ኃላፊነት በአብዛኛው በእናቶች/በሴቶች ላይ የተጣለ ነው፡፡ ከዚህም ሲያልፍ በዓለም ላይ በአሁን ሰዓት 45.4% የሚጠጋው የመደበኛ እና መደበኛ ያልሆውን የአምራች ኃይል የሚወክሉት ሴቶች ናቸው ፡፡

ሴቶች የማኅበረሰባችን የጀርባ አጥንት እንደመሆናቸው ያኅበጣቸው ቀንበር እና ወደኋላ ያስቀራቸው ተግዳሮት ሊቃለልላቸው ይገባል፡፡ ይህንንም ማስፈጸም የሚቻለው የሴቶችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች እና ተግዳሮት የተረዳ ለችግሮቻቸው የሚመጥን መፍትሔ ሲቀመጥ እና ለተግባራዊነቱም በቆራጥነት ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚጠበቅበትን ሲሰራ ነው፡፡ የስርዓተ - ጾታ እኩልነት መርሆችን በመተግበር ለሴቶች የተሻለ ነገን መገንባት የሁሉም ኃላፊነት ሲሆን በግንባር ቀደምትነት ሊይዙት እና ሊያስፈፅሙት የሚገቡት ግን ራሳቸው ሴቶች ናቸው፡፡ ሴቶች በከፍተኛ ሁኔታ በሚሳተፉባቸው/በተሳተፉባቸው የፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ ኪራይ ሰብሳቢነት ይቀንሳል፡፡ የተጋላጭ ማኅበረሰቦች ከለላ ይስፋፋል፡፡ እንዲሁም ለሰላም እና አብሮ ለመኖር ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል፡፡

### የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ

*የሥርዓተ - ጾታ እኩልነት ማለት የሁለቱም ጾታ ሰዎች እኩል መብቶች ፣ ግዴታዎች እና ዕድሎች ሲኖሯቸው ነው ፡፡*

ከላይ በተቀመጠው የስርዓተ - ጾታ እኩልነት ትርጓሜ መስፈርት የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ስንገመግም ሴቶች ያነሱ መብቶች፣ እጅግ የገዘፉ እና የተጋነኑ ግዴታዎች እንዲሁም የተወሰኑ እድሎች ብቻ እንዳሏቸው እንረዳለን፡፡ ይህንን ክፍተት ለመሙላት እና የሴቶችን የዕለት ተዕለት ኑሮ በማሻሻል ለዘላቂ የማኅበረሰባዊ እድገት እና ዘመናዊነት ብዙ ባለድርሻ አካላት ቢኖሩም በዚህ ጹሁፍ ላይ ሴቶች በፖለቲካው ውስጥ ምን መስራት እንደሚገባቸው በተወሰነ መልኩ እናያለን፡፡

የፖለቲካ ተሳትፎ እጅግ ሰፊ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ የፖለቲካ ተሳትፎ የግድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ በመግባት የሚተገበር ላይሆን ይችላል፡፡ የፖለቲካ ተሳትፎ በዓይነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የሄደ ሲሆን በቀጥታ ከመምረጥ እና መመረጥ እስከ ማኅበራዊ ሚዲያ ዘመቻ ይዘልቃል ፡፡ በመሀከልም እጅግ ብዙ የሆኑ የተሳትፎ አይነቶች ይኖራሉ፡፡

ከላይ በጥቂቱ ያስቀመጥናቸው ሴቶች ላይ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን እንደማኅበረሰብ የምንፈታበት መሳሪያ ፖለቲካ ነው ካልን በፖለቲካ ውስጥ ገብተን መሳተፍ የውዴታ ግዴታ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በእኛ ሀገር የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የተለያዩ በደሎች በተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሉ ላይ መፈጸማቸው (ማስፈራራት፣ የዘፈቀደ እስራት፣ የፍትህ እጦት፣ ግድያ) ፖለቲካውን ብዙዎች እንዲፈሩት ያደረገ ሲሆን የዚህ የመገፋት ፖለቲካ ገፈት ቀማሽ የነበሩት ሴቶች ከነበራቸው ጥቂት የፖለቲካ ተሳትፎ ፈርተው እንዲታቀቡ አድርጓቸዋል ፡፡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህግና ደንቦች ውስጥ ሴቶችን ለይቶ ተሳታፊ እንዳይሆኑ የሚከለክል ህግ ባይኖርም (ልናጣራ በሞከርነው ልክ) የሴቶችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች የተረዱ ደጋፊ እና አበረታች ማዕቀፎች ግን በብዛት ተግባራዊ ተደርገው አይታዩም፡፡ የሴቶችን ተሳትፎ ለመጨመር አንዳንድ አስገዳጅ የፓርቲ ውሳኔዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን ለተፈጻሚነታቸውም ሁሉም መተባባር አለበት፡፡ ለምሳሌ ኢዜማ በእያንዳንዱ ምርጫ ወረዳ ለክልል ምክር ቤት እጩ ሆነው እንዲወዳደሩ ከሚቀርቡ እጩዎች ቢያንስ 30 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ አስገዳጅ መመሪያ ያስቀመጠ ሲሆን ይህንንም ለማስፋጸም የእጩ ምልመላ እና ድጋፍ፤ የብሔራዊ እና የምርጫ ▶



▶ ወረዳ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪዎች እዲሁም የምርጫ ወረዳው አመራሮች በተቀናጀ ሁኔታ እንዲሰሩ ይጠበቃል፡፡

### ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ እንዴት ሊሳተፉ ይችላሉ?

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ብዙ እይነት የፖለቲካ ተሳትፎ አይነቶች ቢኖሩም፣ ለዚህ ጽሁፍ የመረጥናቸውን የተሳትፎ ዓይነቶች እና ሴቶች እንዴት ሊሳተፉ እንደሚችሉ እናያለን፡፡

#### 1. በቀጥታ ተመራጭ በመሆን፣

ሴቶች ችግሮቻቸውን የተመለከተ ብዙ አጀንዳ እና ጥያቄ ያላቸው ሲሆን ጉዳያቸውንም ለማስፈፀም ከራሳቸው በላይ ሊመጥን የሚችል ወካይ እንደሌላቸው አውቀው በፖለቲካው ውስጥ ቀጥተኛ ውሳኔ ሰጪ ለመሆን መወዳደር አለባቸው፡፡ በእያንዳንዱ የውሳኔ ሰጪ አካል ላይ የምትቀመጥ ሴት በተሰጣት ኃላፊነት ላይ ውጤታማ መሆን እና ለሌሎች ሴቶች ፈር ቀዳጅ መሆን የሚጠበቅባት ውጤት ሲሆን በአጠቃላይ የስርዓተ - ጾታ እኩልነትን ለማስፈን በሚደረገው ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንድትሆን እድል ይሰጣታል፡፡

#### 2. ድምፅ በመስጠት፣

የፖለቲካው መልካም አጋጣሚ ወይም መጥፎ ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ ሴቶች ላይ ተፅዕኖ ስላለው ከቀረቡ አማራጮች ለሴቶች የተሻለ ጥቅም ይሰጣል ብለው ያመኑበትን የፖለቲካ ድርጅት በመደገፍ እና ለኑሯቸው እና በአጠቃላይ ለሀገር ሰላም እና ደኅንነት አይበጁም ያሏቸውን በድምጻቸው ወደኋላ የማስቀረት ሰፊ አቅም እንዳላቸው በመረዳት ሴቶች ድምፅ በመስጠት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው፡፡ ምንም እንኳን ፖለቲከኞች የሁሉ ነገር ፈላጭ ቆራጭ የሆኑ በመምሰል በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኃይላቸውን ለማሳየት ቢሞክሩም የመጨሻውን ውሳኔ የሚሰጠው ግን ህዝብ ነው፡፡ ሴቶች ደግሞ ከህዝባችን ከ50 በመቶ በላይ የመራጩን ቁጥር ይይዛሉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ትክክለኛው ስልጣን ያለው በነሱ እጅ መሆኑን እና የሚጠቅማቸውን ሊሰይሙ የማይጠቅማቸውን ከስልጣን ሊሽሩ አቅም እንዳላቸው እና መብቱ እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ሴቶች ይህንን ስልጣናቸውን በመረዳትና በቆራጥነት ለመራጭነት መመዝገብ እና በምርጫው ወቅትም ቀድመው በመገኘት ድምፃቸውን ይወክሉናል፤ ጉዳያችንን ያስፈጽሙልናል ብለው ላመኑባቸው እጩዎች መስጠት አለባቸው፡፡ ይህንን በማድረጋችን እኛን የምትመስል ሀገር የመገንባ ዕድል እንፈጥራለን፡፡

#### 3. የምርጫ ዘመቻ አካል በመሆን፣

ሀገራችን ኢትዮጵያ እስከ አሁን ድረስ ስታደርጋቸው የቆየቻቸው ምርጫዎች በሰፊው በህዝብ ዘንድ ተአማኒነት እና ቅቡልነት ያልነበራቸው፣ በገዢው መንግሥት አጭበርባሪነት የተጠናቀቁ፣ የህዝብ ድምፅ በግፍ የተሰረቀባቸው፣ የተቃዋሚ/ተፎካካሪው ኃይል ላይ ከፍተኛ ማስፈራራት እንዲሁም እስር እና እንግልት የተፈጸመበት "ለምን?" ያለው የኅብረተሰብ ክፍል የታፈነበት እና የተጨፈጨፈበት ሆኖ አልፏል፡፡ እንዲህ ያለ ገሀድ የወጣ ህገ ወጥነትን በከፍተኛ ሁኔታ መከላከል የሚቻለው በብዛት ቁጥር ያለው የምርጫ አስፈጻሚን እና ታዛቢን በምርጫው ወቅት ማሰማራት ሲቻል ነው፡፡ የሀገራችን ሴቶችም በሀሳብ ያሸነፏቸውን የፖለቲካ ፓርቲ በማስተዋወቅ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚናን በመጫወት እንዲሁም የምርጫ ታዛቢዎችም በመሆን የህዝብን ድምፅ በማስከበር ወደ ዴሞክራሲያዊ ሀገር ግንባታ እየተንደረደረች ያለችው ሀገራችን ባለውለታ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

#### 4. የሲቪል ማኅበራት አካል በመሆን፣

የሲቪል ማኅበራት በምርጫ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን ሴቶች መብታቸውን ለማስከበር በተቋቋሙ የሲቪል ማህበራት ውስጥ በመሳተፍ የምርጫውን ሂደት ለማሳለጥ በሚደረገው ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚናን መጫወት ይችላሉ፡፡ በዚህም ህዝብ ለምርጫ እንዲነሳሳ በማስተማር ህዝቡ እንዳይመርጥ እና መብቱን እንዳያስከብር እና ምርጫ እርባነ ቢስ እንደሆነ እንዲቆጠር በማድረግ እነሱ የፈለጉት ሀሳብ እና ፖለቲካ ብቻ ነግሶ እንዲቆይ ጥረት የሚያደርጉ እና ራሳቸው ግን ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርጉ አካላትን ሴራ ማክሸፍ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለመብታቸው በተደራጀ መልክ ለመንቀሳቀስ ትልቅ አቅም ይሆናቸዋል፡፡

ሴቶች በማኅበራዊ ህይወታቸው ከፍተኛ ትስስር ያላቸው ሲሆን በእድር እና በእቁቦች ሳይቀር በፖለቲካ መሳተፍ እና የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰንን ኃላፊነት ስለመወጣት በመመካከር ግንዛቤ መያዝ አለባቸው፡፡ በአጠቃላይም የሚኖራቸው የፖለቲካ አቋም እና ድጋፍ መለያየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሳትፎ አድርጎ የዜግነት ግዴታቸውን ስለመወጣት ግን በትብብር መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

#### 5. ማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም፣

ከፍተኛው የፕሮፖጋዳ መሳሪያ እየሆነ የመጣው ማኅበራዊ ሚዲያ በሀገራችን ያን ያህል ከፍተኛ ተጠቃሚ ባይኖረውም ተፅዕኖው ግን እጅግ ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ የተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያ ድህረ ገጾችን የሚጠቀሙ ሴቶች መብቶቻቸውን ወደኋላ የሚመልሱ እንዲሁም ለሀገር ሰላም እና አንድነት ጠንቅ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን በአፅንዖት መከታተል እና ማጋለጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በዘመናት የሀገራችን የፖለቲካ እና ማኅበራዊ ሂደት የሴቶች የትምህርት ተደራሽነት እጅጉን አናሳ ሲሆን እድሉን አግኝተን ትምህርት የቀሰምን እና ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ መጠቀም የቻልን ሴቶች ወደኋላ የቀሩትን የሀገራች ሴቶችን ድምፅ ወክለን መታገል አለብን፡፡ በዚህም ሂደት ውስጥ መረጃው የሌለንና እውነትነቱን ያላረጋገጥነውን ጉዳይ ባለማጋራት ከተቻለም በማጋለጥ ከፊታችን ያለውን ምርጫ ዴሞክራሲያዊ እና ሰላማዊ ለማድረግ አብረን በጋራ እንስራ፡፡

### ማጠቃለያ

ከግማሽ በላይ የሆነውን የማኅበረሰብ ክፍል ያላሳተፈ ማንኛውም የፖለቲካ ሂደት አንካሳ ሲሆን ይህንን የማኅበረሰብ ክፍል ግምት ውስጥ ባለማስገባት የሚደረጉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውጤታማነታቸው እጅጉን የተወሰነ ይሆናል፡፡

ውድ የሀገራችን ሴቶች፡- በሀገራችን በተከሰቱ ማናቸውም አይነት የፖለቲካ ቀውሶች የመጀመሪያው እና ግንባር ቀደም ተጠቂዎች እናንተና ልጆቻችሁ ናቸው፡፡ ይህንን ሂደት ‹‹በቃ!›› የምትሉበት እና በፖለቲካው ሂደት ውስጥ ባለድርሻ የምትሆኑበት ጊዜ እየራቀ እና ከዓይን እየተሰወረ እንዳይሄድ ዛሬውኑ "በሀገሬ ጉዳይ ላይ እኔም ያገባኛል!" ብላችሁ ተነሱ፡፡ የምትለፋላቸው ሕጻናት በሀገራቸው ብሩህ ተስፋ እንዲኖራቸው፣ አዕምሯቸው ነፃ ሆኖ የተለያዩ ፈጠራዎችን ስለመፍጠር እንጂ ስለስደት እንዳያስቡ፣ ስለተስፋ እንጂ ስለጦርነት እንዳይሰሙ፤ ዛሬ እናንተ ጉዳዬ ነው ብላችሁ በፖለቲካው ውስጥ ተሳተፉ፡፡ አንድ ላይ በመሥራት እኛን የምትመስል ሀገር እንገንባ፡፡

# በአልነጃሺ መስጅድ ላይ የደረሰው ጥቃት በገለልተኛ አካላት እንዲጣራ ኢዜማ ጠየቀ

ታኅሣሥ 28 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአልነጃሺ መስጅድ ላይ የደረሰውን ጥቃት በገለልተኛ አካላት በፍጥነት እንዲጣራ፣ ጥንታዊ ቅርስነቱን ሳይለቅ መስጅዱ ወደነበረበት ሁኔታ በፍጥነት እንዲመለስ ለዚህም ሲባል መላው ሕዝብ ሙስሊም ክርሰቲያን ሳይል ተደጋግፎ ተገቢው ጥገና ለማድረግ የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪውን አቀረበ፡፡

ኢዜማ፣ ታኅሣሥ 26 ቀን 2013 ዓ.ም በሕዝብ ግንኙነት ክፍሉ በማኅበራዊ ትስስር ገጽ በኩል ባሰራጨው መግለጫ፣ ‹‹ይህን መጥፎ የታሪክ አጋጣሚ እንደተለመደው ሁሉ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እና ክርሰቲያኖች በችግራቸው ጊዜ በጋራ የሚቆሙ መሆናቸውን በሠርቶ ማሳያነት እንዲጠቀሙበት›› ሲል ጥሪውን አቅርቧል፡፡

እ.ኤ.አ 1954 የተባበሩት መንግሥታት የሰላም መደፍርስ ባለበት ሁኔታ ሀገራት በተናጠልም ሆነ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በጋራ ቅርሶችን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ዓለም አቀፍ ድንጋጌ መውጣቱን የጠቀሰው ኢዜማ፣ ዓለም አቀፉ የቀይመስቀል ማኅበርም በ38ኛ ድንጋጌው በግጭት ውስጥ ያሉ ማናቸውም አካላት ለእንዲህ አይነት ቅርሶች ከለላ እና ጥበቃ እንዲደረግ የሚያዝ መሆኑን ጠቁሟል ፡ ፡ ኢትዮጵያ የእነዚህ ሁለት ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ፈራሚ ከሆኑ ሀገራት አንዷ መሆኗን ያስታወሰው ኢዜማ፣ ከዓለም አቀፍ ሕግ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ በዚህ ታላቅ መስጅድ ላይ ጉዳት በመድረሱ የተሰማውን ጥልቅ ሐዘን ገልጿል፡፡

ሀገሪቱ በዘላቂነት ከእንዲህ ያለ አፍራሽ ሁኔታ ፈጥና እንድትወጣ ሕዝቡም አምባገነንነትን እንዲጸየፍ፤ በየትኛውም ጊዜ በሀገሪቱ የሥልጣን ማማ ላይ የሚወጡ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች የሃይማኖት ተቋማት የሀገሪቱን አብሮነት፣ ታሪክና ልማት የማዕዘን ድንጋዮዎች መሆናቸውን በመረዳት ለሁሉም አብያተ ዕምነቶች፣ ምእመናን እና ለየዕምነቶቹ ሀገራዊ ቅርሶች ተገቢውን ክብር፣ ከለላ እና እኩል ጥበቃ እንዲያደርግ ኢዜማ ጠይቋል፡፡

# በኢዜማ ሥር ያሉ ምርጫ ወረዳዎች የምርጫ አስፈጻሚዎችን ገለልተኝነት ለማጣራት ዝግጁ ሆነው እንዲጠብቁ ጥሪ ቀረበ

ታኅሣሥ 28 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተሰፋዬ፣ የኢዜማ ምርጫ ወረዳዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ዝርዝር በሚልክበት ጊዜ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ገለልተኝነት ለማጣራት ተገቢውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ጥሪ አቀረቡ፡፡



ኃላፊው፣ ከተለያዩ መዋቅሮቻችው ከምርጫ አስፈጻሚዎች ጋር በተያያዘ የማይመለከታቸው አካላት የምርጫ አስፈጻሚ ምልመላ እያካሄዱ ነው የሚል ጥቆማ ደርሷቸው እንደነበር ጠቅሰው፤ ይህንን የሚያስረዳ ሰነድ አያይዘው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ደብዳቤ ጽፈው እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ ‹‹ምርጫ የማስፈጸም ሥራ በአዋጁ እንደተቀመጠው ኃላፊነቱ የምርጫ ቦርድ ነው›› ያሉት ዋሲሁን ተሰፋዬ፣ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ከወጣ በኋላ የቦርዱ ሰብሳቢ በተገኙበት የምርጫ አስፈጻሚዎችን በተመለከተ ውይይት መደረጉን ጠቁመዋል፡፡ በውይይቱም ላይ ሁለት አበይት ነጥቦች መነሳቱን ጠቅሰዋል ፡፡ የመጀመሪያው ነጥብ ከዚህ በፊት ምርጫውን ሲያስፈጽሙ የነበሩ የምርጫ አስፈጻሚዎች ከዚህ በኋላ የማይቀጥሉ መሆኑን ሲሆን፤ ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ ተካሄዶ ከተጠናቀቀ በኋላ ለፓርቲዎቹ የምርጫ አስፈጻሚዎቹ ማንነት ተልኮ ፓርቲዎች ሀሳብ ከሰጡበት በኋላ የምርጫ አስፈጻሚዎቹ የሚመረጡ መሆኑን ኃላፊው አስረድተዋል፡ ፡ ‹‹ይህም ይሆናል ብለን እንጠብቃለን፡፡ እኛ ይህ እንደሚሆን የምናጣራው በምርጫ ወረዳዎቻችን በኩል ነው፡፡ በምርጫ ወረዳዎቻችን ሥር ያሉ አመራሮች ለዚህ ዝግጅት በማድረግ ገለልተኝነታቸውን በትክክል እንዲያጣሩ እናደርጋለን፡፡ የወረዳዎቻችን አመራሮችም ለዚህ ተገቢውን ዝግጅት እንዲያደርጉ›› ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

‹‹ምርጫ ቦርድ የሚያስተላልፈውን ስም ዝርዝር በጠቅላላ የማጣራት አቅሙ አላችሁ?›› በሚል ከዜጎች መድረክ ለተነሳው ጥያቄ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው በሰጡት ምላሽ፡-

ከ435 በላይ የምርጫ ወረዳዎች ላይ መዋቅር እንዳላቸው ጠቅሰው፣ ምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈጻሚዎቹን እንደላከላቸው ባላቸው መዋቅር መሰረት ወደየምርጫ ወረዳዎቻቸው ስም ዝርዝሩን ልከው ተገቢውን ማጣራት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚያጠናቅቁ ገልፀዋል፡፡

‹‹ምርጫ አስፈጻሚነት ገለልተኝነትን የሚጠይቅነው፡፡ ምርጫ ቦርድ የመለመላቸው ሰዎች የፖለቲካ አመለካከታቸው ምንድነው? የሚለውን ነው በምርጫ ወረዳ መዋቅሮቻችን ባሉ አባላት አማካኝነት የማጣራት ሥራ የምንሰራው›› ያሉት ኃላፊው፣ ኢዜማ ካለው ሰፊ መዋቅር አንጻር ይህንን ማጣራት ከባድ ሥራ እንደማይሆንባቸው አስታውቀዋል፡፡





# ኢዜማ ከ2013 ዓ.ም ምርጫ የሥነ - ምግባር መመሪያ አወጣ

ታኅሣስ 28 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የምርጫ ስትራቴጂና ሜኔጅመንት ኮሚቴ የኢዜማ አመራር፣ አባላት፣ ደጋፊዎች፣ የምርጫ እጩዎችና የኢዜማ ምርጫ ታዛቢዎች የሚሳተፉበት የ2013 ዓ.ም ምርጫ የሥነ - ምግባር መመሪያ ማውጣቱን አስታወቀ፡፡

ዘንድሮ የሚካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሀገራዊና ታሪካዊ ፋይዳ በማየት በቀጣይ ኢዜማ ሊያደርገው የሚገባው አቅጣጫ በማስቀመጥ እና ሀገራዊ ፋይዳውን በመተንበይ በምርጫው ላይ ኢዜማ መሳተፍ የሚገባው እና መከተል የሚገባውን የሥነ ምግባር መመሪያ በግልጽ የሚያስረዳ፤ አባላቱ እና አመራሩ እንዲሁም ኢዜማ በመጪው ምርጫ አሸንፎ እንዲወጣ የሚፈልጉ ደጋፊዎች ጭምር እንዲመሩ የሚያደርግ ለአያያዝ አመቺ በሆነ መልኩ የሥነ ምግባር መመሪያው በማውጣት በሥራ አስፈጻሚ ማጸደቃቸውን፣ መመሪያውም በቅርቡ ለሁሉም ተደራሽ እንደሚደረግ የኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂ ማኔጅመንት ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ከውሰር እድሪስ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

የኢዜማ አመራሮች፣ አባላት፣ የኢዜማ ምርጫ ታዛቢዎች እንዲሁም ደጋፊዎች እንደማንኛውም ሰው ከምርጫው ጋር በተያያዘ ከመንግሥትና ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር አለመግባባት ቢነሳ በተመሳሳይ መልኩ ምላሽ እንዳይሰጡ፤ ሌሎችንም ተንኩሰው ችግር ውስጥ እንዳይገቡ የምርጫውን ደንብ አክብረው እንዲንቀሳቀሱ ታስቦ በምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ በኩል የተዘጋጀውን ሰነድ ለኢዜማ አባላት፣ ለተወዳዳሪ እጩዎች፣ ለብሔራዊና ለክልል ምርጫ ዘመቻ አስተባባሪዎችና ባለድርሻ አካላት ሰፊ ሥልጠና እንደሚሰጥ የጽህፈት ቤት ኃላፊዋ ጠቁመዋል፡፡

ኢዜማ ያወጣው የሥነ-ምግባር መመሪያ ደንብ የፓርቲዎች የቃል ኪዳን ሰነድ፤ የሀገሪቱ የምርጫ ሕጎችና ደንቦች በሙሉ እንዲያከብር ተደርጎ መውጣቱን፤ የወጣው የሥነ ምግባር ደንብ እስከ ምርጫው ፍጻሜ ተግባራዊ እንደሚሆን ይሄን የሚጥሱ ካሉ በቅድሚያ በምርጫ ወረዳ ደረጃ የእርምት እርምጃ እንደሚወሰድ፤ ምርጫ ወረዳው ያቃተው ጉዳይ ካጋጠመ በ ዲስፕሊን ኮሚቴ በኩል ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን ኃላፊዋ አስረድተዋል፡፡

‹‹የኢዜማ አባላት፣ አመራሮች እንዲሁም በምርጫው ላይ የሚሳተፉ አካላት በቅድሚያ የወጣውን የሥነ-ምግባር መመሪያ ማክበር ይገባቸዋል›› ያሉት የኢዜማ ምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ከውሰር እድሪስ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ተፎካካሪን ከመተንኮስ የጥላቻ ንግግርን ከመጠቀም እንዲሁም የሚያጋጭ ቃላት ከመጠቀም መቆጠብ አለባቸው ብለዋል፡፡

# ‹‹እንደ ኢዜማ ፖሊሲዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች መኖራቸውን እጠራጠራለሁ››

## አማን ይኹን ረዳ የኢዜማ ፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪ

ታኅሣሥ 28 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)








የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ እና የከተማ ልማት ፖሊሲውን ታኅሣሥ 25 ቀን 2013 ዓ.ም በዋና ጽሕፈት ቤቱ በመስፍን ወልደ ማርያም አዳራሽ ለውይይት አቀረበ፡፡ ኢዜማ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳሉ ያላቸውን ከ40 በላይ ፖሊሲዎች በባለሙያዎች ያዘጋጀ ሲሆን፣ ከእነዚህም መሀል የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲውንና የከተማ ልማት ፖሊሲውን የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና ጥሪ ለተደረገላቸው ባለሙያዎች ነው ለውይይት ያቀረበው፡፡

የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አስተባባሪው መሳይ ግርማ የሕዝብ ቁጥር ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ገልጸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቁጥር ከ115 ሚሊዮን በላይ መድረሱን ጠቁመዋል፡፡ በየዓመቱም 2.5 ሚሊዮን የሚሆን አዲስ ሥራ ፈላጊ ወጣት ገበያውን እንደሚቀላቀል የገለጹት የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አስተባባሪው፣ ፖሊሲ በመቅረጽና ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ችግሩን መቅረፍ እንደሚቻል አስረድተዋል፡፡ ‹‹የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ በመንግሥት ተዘንግቷል›› ያሉት የፖሊሲ አስተባባሪው፣ የሚመለከታቸው አካላት እየተማከሩ በጋራ እየሰሩ እንዳልሆነ ጠቁመው፤ ኢዜማ የህጻናት፣ የወጣቶች እና የእናቶች የሞትን መጠን መቀነስ፣ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

በውይይቱ ላይ ከባለሙያዎችና ከኢዜማ አባላትና አመራሮች ጥሩ ግብዓት መገኘቱን የጠቆሙት የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አስተባባሪው፣ የሕዝብ ጉዳይ ብቻውን መነሳት ያለበት ነገር ባለመሆኑ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ከጤና፣ ከግብርና፣ ከትምህርት እና ከከተማ መመሥረት ጋር ስለሚያያዝ ኢዜማ ከሚያዘጋጃቸው ሌሎች ፖሊሲዎቹ ጋር መጣመርና መጣጣም ይገባዋል ብለዋል፡፡ ‹‹እንደ ኢዜማ ፖሊሲዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች መኖራቸውን እጠራጠራለሁ›› ያሉት የኢዜማ የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪ የሆኑት አማን ይኹን ረዳ፣ ፓርቲያቸው ፖሊሲውን በቀረጸው መልክ ወደ ሕዝብ የሚያወርድ መሆኑንና ፖሊሲዎቹ የተቀረጹት ለፖለቲካ ትርፍ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር ለመፍታት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

‹‹ፖሊሲ አለቀለት፤ እንከን የለሽ ነው አይባልም›› ያሉት የፖሊሲ አስተባባሪው፣ ኢዜማ የቀረጸው ፖሊሲ በየጊዜው የሚሻሻል ከሚመጣው ለውጥ ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ማሻሻያዎች እንደሚደረግበት፤ ኢዜማ አሸንፎ ሥልጣን የሚይዝ ከሆነ ፖሊሲውን ሥልጣን እንደያዘ ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

‹‹ፖሊሲዎቹ መቼ ይጠናቀቃሉ? ለሕዝብስ መች ይፋ ይሆናሉ?›› ብላ የዜጎች መድረክ ለጠየቀቻቸው ጥያቄ የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው በሠጡት ምላሽ እስከ ጥር 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ፖሊሲዎቹ ተገምግመው እንደሚጠናቀቁና የኢዜማ ኮንፍረንስ ካጸደቃቸው በኋላም ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆኑ ገልጸዋል፡፡





# ኢዜማ፣ ፋይናንስን በተመለከተ በአዲስ አበባ ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት ሥልጠና ሰጠ

ታኅሣሥ 28 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)





የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ ለሚገኙ የኢዜማ ምርጫ ወረዳ ሊቀ መንበሮች፣ ትሬዠረሮችና የፋይናንስ ኃላፊዎች የፋይናንስ አሰራርን የተመለከተ ሥልጠና መስጠቱን የኢዜማ በጀትና ፋይናንስ ኮሚቴ ኃላፊ አንድነት ሽፈራው ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

የሥልጠናው ዓላማ ከምርጫው ጋር በተያያዘ የሚሰባሰቡት ሀብትና ግብዓት፣ የተሰበሰቡትም ጥቅም ላይ ከመዋላቸውና ሥራውም ከመጀመሩ በፊት ተገቢውን የሰነድም፣ የአሰራርም እንዲሁም የሰው ኃይልም ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ያንን ለሚመለከታቸው አባላት ለማስረዳት መሆኑን ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

ፓርቲያቸው ከሥልጠናው በፊትም ቢሆን በአፈጻጸም ደረጃ ጥሩ ውጤት እያስመዘገበ እንደሚገኝ የገለጹት የፋይናንስ ኃላፊው፣ ኢዜማ አዲስ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ ተግዳሮቶች እንደገጠሟቸው ጠቁመዋል፡፡ እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታትም አሰራራቸውን በተገቢው መልኩ በውይይት በማስረዳት ያለባቸውን ችግር እየቀረፉ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

ኢዜማ፣ የሰጠውን ፋይናንስ ተኮር ሥልጠና በቀጣይነት በክልል ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በዋና ዋና ከተሞች ተደራሽ ለማድረግ እንደሚሰራ ለማወቅ ተችሏል፡፡